# እንዴት ሰው ይሞታል?

**እንዴት ሰው ይሞታል?**

ታጋይ ሆኖ ሲኖር
እንዲሻሻል አገር
**እንዴት ሰው ይሞታል?**
ፍሬውን ሳይበላ፣ እልል! እልል! ሳይል?
ውኃ እህል ቆጥቦ፣ ሲወጣና ሲወርድ
ሲኖር በሰው አገር፣ አገሩ እንዲሻሻል።
ሁሌ ሲይንገላታ፣ በዚያ በሰው አገር
ስደቱን ሳይረግም፤
በተስፋ እየኖረ ለሚሻለው ዓለም።
**እንዴት ሰው ይሞታል?**
ማተቡን ሳይበጥስ፤
ቃል ኪዳንም ሳይጥስ።
ይገርማል ይደንቃል
ሳላየው፣ ሳልጠይቀው፣ በሐሳብ አወቅሁት፤
በታገለውና በለፋበት ልፋት፣
እንዲሻሻል አገር፣ በረገጠው መሬት።
**እንዴት ሰው ይሞታል?**
ታጋይ ሆኖ ሲኖር
ለማሻሻል አገር፤
አለፈ እንደ ጊዜ
ተሸክሞ ሚሥጥር።
**እንዴት ሰው ይሞታል?**
የወንድሜን ነፍሥ ይማር እኔ ልበልለት፤
ባንጋራም እንኳን የሰማይን እምነት።
ብርሃኑ ወገኔ
ደግሞም ላወድስህ፣
ሌት ከቀን ስለጣርህ፤
ለውዷ አገርህ።

ለአቶ ኢብራሂም አብዱልቃድር (ብርሃን) መታሰቢያ
ከለምለም ፀጋው April 2014